

በ: ኦራ አያል
ምሳሌዎች: ኦራ አያል
הוֹצָאָה: ספרית פועלים
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

קְרִיאָה

ለቤተሰባዊ ንባብ የሚጠቅሙ ምክሮች
ብዙዎቹ ለታዳጊ ህፃናት የሚዘጋጁ መጻህፍት ታሪኩን እንዲከታተሉና ንባብን እንዲቀላቀሉ የሚረዳቸው ተደጋጋሚ‘‘ ዓረፍተ ነገር አላቸው። ታሪኩን በሚያነቡበት ጊዜ የሚደጋገሙትን ዓረፍተ ነገር ለማጉላት በልዩ ድምጽ ማንበብ፣ የእጅ እንቅስቃሴዎችን መጨመር ወይም የንባብ ዘይቤን መቀየር ትችላላችሁ። የተለመደው ዓረፍተ ነገር ወደ እነርሱ ሲመጣ ታዳጊዎቹ ከእናንተ ጋር በመገናኘታቸው ደስተኞች ይሆናሉ።
ኦራ አያል (1946-2011) – የልጆች ሠዓሊትና ደራሲት ናት። የሚርያም ሩት የታወቁትን መጽሃፎችንና እራሷ የደረሰቻቸውን ማለትም፦ ‘ብቻዋን የሆነቺው ልጃገረድ’፣ ‘አንድ ጨለማ ምሽት’ና ሌሎችንም ጨምሮ ከ70 በላይ ‘‘ የህፃናት መጽሃፎችን ምስል አዘጋጅታለች።

שִׂיחָה

?ውይይት - ማንን ነው መጎብኘት የምንፈልገው
ጉብኝቶች የታዳጊ ሕፃናት ዓለም ጉልህ ክፍል ናቸው። ዘመዶቻችንንና ጓደኞችን ለመጠየቅ እንሄዳለን። አንዳንድ ጊዜም እኛን ሊጠይቁን ይመጣሉ። መወያየትና መጠየቅ የምትችሉት፦ ማንን ለመጎብኘት ሄድን? በጉብኝቱ ወቅት

?ምን አደረግን? ወደ ቤታችን ማንን እንጋብዛለን

שִׂיחָה

?አሁን ማንን እናገኛለን
በእያንዳንዱ ገጽ መጨረሻ ላይ በሚቀጥለው ገጽ ላይ ስለምናገኘው ነገር የሚጠቅስ ምስል አለ። ገጹን ከመግለጣችሁ በፊት የተገለጸውን ፍንጭ መመልከትና በሚቀጥለው ገጽ ላይ ማን እንደሚጠብቃችሁ መገመት ትችላላችሁ።
እንዲሁም በእውነተኛ እቃዎች መጫወት ትችላላልችሁ – አንድን ነገር ከሞላ ጎደል በመሸፈን ታዳጊዎቹን ከሽፋን ስር ?ምን እንደተደበቀ መጠየቅ – የቴዲ ድብ፣ ኮፍያ ወይስ ምናልባት ትንሽ ቦርሳ

כְּלָלִי

?በምስሉ ውስጥ ምን አለ
የመጽሐፉ የመጨረሻ ገጽ ብዙ ሥዕላዊ መግለጫዎች ያሉት በራሱ ታሪክ የሆነ ነው። በታሪኩ ውስጥ ያገኛችሁትን ምስል መፈለግ ትችላላችሁ -ውሻ፣ ሴት ልጅ፣ ኮፍያ ወይስ አበባ። እንዲሁም በአያት ቤት ውስጥ ያሉትን ነገሮች ?ለመለየት መሞከርና በስም መጥራት ትችላላችሁ፡- ማፍያው የት ነው? ግድግዳው ላይ የተንጠለጠለው ምንድን ነው

הַשְׁרָאָה

פינטרסט
[ተጨማሪ አስገራሚና የሚመከሩ ልዩ ነገሮችን በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ ታገኛላችሁ።]